★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 34 ቁ. 2 ጥቅምት 2001 ዓ.ም.

## ሀገር ማዳን በዴሞክራሲ ለዴሞክራሲ

*ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ በህልውናዋ ላይ ከፍተኛ አደጋ እያንዣበባት ያለች ሀገር ናት ብንል ትክክል ነው:: የአደጋው ምንጭ የወያኔ አገዛዝ ሀገር አውድም ፖሊቲካውና ድርጊቱ መሆኑ ደግሞ ክርክርን አይጋብዝም:: ከደደቢት የወጣው ይህ መርዘኛ ሕዝብን ከፋፋይ ቡድን ላለፉት 34 ዓመታት ሀገራችን ኢትዮጵያን ሊያጠፋ ቀን ተሌት ሲባዝ መቆየቱም የሚታወቅ ነው:: ሁሉም ብሔረሰብ ይገንጣጠልና የራሱን ነፃ መንግሥት ያቋቁም፤ የአማራ ሕዝብ ጠላታችን ነው ብሎ የተነሳው ወያኔ የጠባብነት መርዙን በትግራይና አልፎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲረጭ ቆይቷል:: ለዚህም ነው ዛሬ ወደ ውድቀቱ እያመራ ባለበት ደግሞ የክፍፍልና የጦርነት ፈንጂዎችን ኢትዮጵያ ላይ አጥምዶ እየተዘጋጀ ያለው:: ለዚህም ነው ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ሀገራችንን የማዳኑ ተልዕኮ ዋነኛ ቀዳሚ ሆኖ ይገኛል የምንለው::*

*ሀገርን ለምንስ ማዳን ያስፈልጋል ብለን በበኩላችን ጥያቄ የምናነሳ ወይም ድርድርና ክርክር የምንገባ አይደለንም:: ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት የሚለው ለእኛ ባዶ ቃል፥ መና ስሜት አይደለም:: ለብዙሃኑ ባትመቸንም፥ ለገዳዮቻችን እየተመቸች ብታበሳጨንም፥ የሚሞቱላትን የዘነጋች መስላ ብትታይም፥ ብዙሃኑ ባንከብርባትም እናት ሀገራችን ናትና ሰቆቃና መከራዋ ያመናል:: ህልውና ሲደፈር፥ ስትቆራረጥ ያበግነናል፤ ስትወረር ስትደፈር ደማችን ፈልቶ ይፈስላታል:: ሀገር ወዳድ ነንና፥ ከባንዳና ከሀዲ የተለየ ነንና፥ ሀገራችንን ለማዳን ውድ ሕይወታችንን እንሰጣለን፤ እንገብራለን:: ይህም ያኮራናል፤ ያስደስተናል እንጂ አያሳዝነንም፤ አያሸማቅቀንም:: ሀገርን የምናድነው ለራሳችንም ለመጪውም ትውልድ ነው:: ደማቸውን አፍሰው የቀድሞዎቹ ያስረከቡንን ሀገር እኛ በእኛ ጊዜ አስጠቅተንና አስገንጥለን፤ አፈራርሰን ለመጪው ትውልድ ውርደትና ስደትን፤ በገዛ ሀገሩ ባዳነትን ልናወርስም የሚጠበቅ አይደለም:: የፍልስጤም ሕዝብ ሰቆቃ፤ የሶማሊያ ሕዝብ መከራ፤ የሶቭየት ሕብረትና የዩጎስላቪያ መፈራረስ*

የኢትዮጵያ እንዲሆን ሕይወትና አቅም እስካለን ድረስ ልንፈቅደው የሚሆን ክስተት አይደለም። ሰው መከበሩ በአገሩ÷ በድንበሩ የተባለውን ያስታውሷል።

ናቅፋ ተረግዞ ደደቢት የተወለደው ጉድ ሀ ብሎ ሲጀምር፤ በኢትዮጵያ ላይ ጉግ ማንጉግ ሆኖ የተቃኘ ነበርና የግንጠላና የእርስ በርስ ጥላቻን ተግቶ በማሰራጨት ሀገር ሊያጠፋ ዳከረ ። የኢትዮጵያን ጥፋት የሚመኙ የሩቅም ሆኑ የቅርብ ጠላቶች በዚሁ ተባበሩት። እንግሊዝ አሜሪካ÷ ሱዳን÷ ሊቢያ÷ የውስጥ ጠባቦች ወዘተ... አጋር ሆነውት ቆሙ። የሕዝብን አብዮት ማጅራት መትቶ ለሥልጣን የበቃው ፋሽስታዊ የመኮንኖች አገዛዝ ደግሞ ሀገር ወዳድ ኃይሎችን በመጨፍጨፍ የፖለቲካ መድረኩን ለሀገር አጥፊ ጠባቦች አመቻቸ። ወያኔም በሌሎች እየተረዳ በኢሕአፓ ላይ÷ በኢዲኅ ላይ÷ በሀገር ወዳድ የትግራይ ተወላጆች ላይ ሳይቀር ዘመተ። ታሪክን ማጥፋት ለጠባብ ተልዕኮአቸው አስፈላጊም ነበርና በኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያ ብለው የታገሉትንና ለጠባብ ብሔርተኝነት ጆሮ አልሰጥ ያሉትን በቀጥታም በራሱ ሆነ በቀይ ሽብር አራማጆች አማካይነት በሰርጎ ገቦቹ አስፈጀ። ታሪክ አዋቂና ሀገር ወዳድ ሲጠፋ ባንዳና ከሀዲው መፈንጨያ ያገኛልና ነው። ያኔ በዚያ የግብግብና ወሳኝ ትግል ወቅት፤ ኢሕአፓ ይህን የጠባብ ቡድን ገና ከውልደቱ ፤ ይህ ጉድ አረመኔና ሀገር አጥፊ ነው ብሎ ሲታገለው የሩቅ ታዛቢና የሆኑና በወንድሜ ግንባር ደም አልይበት ማለት ሲገባቸው መበርከት መሰንበት ብለው የፈሪ ኑሮን ታቅፈው የቆዩ ግን ዛሬ ጅብ ከሄደ ዓይነት ኡኡታቸውን የሚያቀልጡትንም ማስታወስ የግድ ይሆናል። ሀገርን በአንድነት መጠበቅ ሲገባ÷ ይህም አንድነት ስለተመኙት አለሁ እነሆ የሚል ሳይሆን ዴሞክራሲ መስፈንን÷ እኩልነት መረጋገጥን÷ ትግልን ይጠይቃል ያሉትን በማውገዝ÷ ጭቆና ተወግዶ ሀገርን በዴሞክራሲና በፍቅር በጋራ እንጠብቃት ያሉትን በመኮነን የተሰማሩ ሀገርን ሊጠብቁ ቀርቶ ለአፍራሾች መንገድ ጠራጊ ሆኑ። የኮለኔሉ አገዛዝ በጭፍጨፋ አንድነትን ሊያስከብር እንደማይችል ቢነገርም÷ ይኸ ለምን ተባለ--ተጠቆመ፤ ጭቆና ይጥፋስ ለምን ተብሎ ባዮች በርክተው ያኔም ዛሬም ይህን የሀገር ማዳን ትግል አስቸጋሪ እያደረጉት አሉ። ኢሕአፓ የጠባቦችን ሴራ እየታገለና ለማክሸፍ የደም ዋጋ እየገበረ በዚያውም መብት ይከበር÷ ጭቆና ይወገድ አሊያም ለጠባቦቹ ለም መሬት እንሰጣለን በማለቱ ቀናውን ብንነግረው ወልግድግዱን አለ እንደተባለው ጠባቦቹ በትምክህት ሲከሱት ሌሎቹ ደግሞ ሀገር ሊያስገነጥል ብለው ወነጀሉት። ዛሬ መለስ ብለን ስንቃኝ ግን ኢሕአፓ ያቀረበው መፍትሔ፤ የፌዴሬሽን አማራጭ፤ የዴሞክራሲና የእኩልነት መንገድ የተሻለና ሀገር አዳኝ እንደነበር መገንዘብ እንችላላን። ዛሬ ሲነጋ ሌሊቱ ወይም ጉዱ ፈልቶ ከፈሰሰ በኋላ ሀገር ወዳድ ከእኛ በላይ ለአሳር ባዮች በተገላቢጦሹ የኢሕአፓን ኢትዮጵያዊነት ሊጠራጠሩ ቢነሱም፤ ለሀገሩና ለሕዝብ ሲል መከራን የተቀበለውና መስዋዕትን የከፈለው ኢሕአፓ፤ ኢትዮጵያ ምስክሬ ናት ሲል አሌ ሊለው የሚችል ባለ ሐቅ ጨርሶ የለም።

ሀገርን ማዳን ለመጪው ትውልድ የሚለጉት ሐኬት አይደለምና እያንዳንዱ ትውልድ ግዳጁን መወጣት አለበት። የአፍ አርበኛ÷ የሶፋ ፋኖ ሀገርን አያድንምና ጠመንጃን ወድሮ ትግሉ ነው

ህይወቴ ለኢትዮጵያ እናቴ ብሎ መነሳትንና ሞትን ማን ሊፈራሁ ማለት ይገባል:: ይህን ግዳጅ ደግሞ ደጋግሞ ማሳሰብና መጠቆም ብቻ ሳይሆን፤ ግዳጁን ተቀብሎ ኢሕአፓ ትላንትም ዛሬም በትግሉ መድረክ ፀንቶ በመቆም፥ ለማንም ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ሳይጎነበስ፥ የሀገርን ጥቅም ለባዕድ አሳልፎ ሳይሰጥ፥ የሀገር አድን ትግልን ቀንዲል እንዳይጠፋ ተንከባክቧል፤ ራሱም ነዷል:: የወያኔ አረመኔ አገዛዘ ጥላ ሲያጠል በግንቦት 1982 ባሰራጨው ዴሞክራሲያ (ቅፅ 16፤ ቁጥር 2) የሚከተለውን አስፍሮም ነበር፤

> " ረሐብ፤ ቸነፈር፤ ኃዘን ሰቆቃው ኢትዮጵያን ዓፅመ ርስታቸው አድርገው ለሀገሪቷ መጠሪያ ሆኑ:: አንድ ሀገር ከዚህ በታች የምትወርድበት የድቀት ወለል መኖሩ ያጠራጥራል:: ተእንግዲህ ለኢትዮጵያ የሚቀራት ሀገር የመሆን ያለመሆን ጥያቄ ነው:: መልሱ ሀገሩን ሀገር ለማድረግ የሚሻ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊን ሁሉ የግድ የሚያገባው ነው...
> በጥንታዊ ሥልጣኔዋ፤ በነፃነት አምድነቷ አሻቅበው የሚያይዋት፤ የሚኮሩባት፤ ተገን የምትሆን ሀገር መሆኗ ቀርቶ የመጨረሻይቷ ኃላ ቀር ፤ ነዳይ ምስኪንና ምፅዋተኛ፤ የሁከት መናኸሪያ፤ የእድገት መቀበሪያ ሁና፥ ቁልቁል በአድንኖ፥ ዓይንን ሰብሮ ለሚመለከቷት፥ ትቢያ ላይ ስለወደቀች ሀገር ቁጭት ለሚሰማው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የጓዳውን ጣጣ ፈንጣጣ ፥ የትግሉን አንጃ ግራንጃ ወደ ዳር ትቶ፥ ትቢያዋን አራግፎ፥ ርስሐቷን ከልቶ፥ በትር ምርኩዝ ሁኖ በእግሯ ተደላድላ እንድትቆም አድርጎ ሀገር አለኝ ለማለት መብቃት፥ የቀረበለት ቁልጭ ያለ የሞት ሽረት ጥያቄ ነው:: ከዚሁ ሀገርን እንደ ሀገር ከማቆም ጥያቄ ጋር አብሮ መመለስ ያለበት ይህችው ሀገር ቆማስ ወዴት ነው፥ በምንድነው የምትራመደው የሚለውም ጭምር ነው:: ኢትዮጵያ ጤና እንድትገዛ፤ ሕዋሳቷ ሕይወት አግኝተው እንዲነዝሩ፤ እጆቿን ወደ ጥበብ አድማስ እንድትዘረጋ፤ ያለ መሰናክል በእድገት ጎዳና እንድትራመድ ኋላ የቀረችውን ያህል አንድትገሠግስ፤ አመንምኖ ከዚህ ድቀት የጣላትን..መዳረሻ ማጥፋትና ዳግመኛም የማይመለስብትን መላ መምከር የግድ ነው "::

ይህ የኢሕአፓ ምክር ሆነ ማሳሰቢያ ብዙ ሰሚ ባለማግኘቱ መምከር መዘጋጀት መታገል የነበረበትም ግዳጁን ባለመወጣቱ ወያኔ በላያችን ላይ ሊሰየምና ዳግም በጦርነትና ሁከት ማጥ ሊከተን ቻለ ::

ሀገርን ለማዳን ስንል ከማንና እንዴት የሚለውም መነሳቱ የማይታለፍ ነው:: አድነናትስ ወዴት ወይም በእግሯ ቆማስ ወዴት ልትጓዝ የሚለውም መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው:: ይህ የሚድበሰበስ ጉዳይ ሊሆን አይችልም:: ኢትዮጵያን የምናድናት ከወያኔ አገዛዝ የጥፋትና የግንጠላ፤ የጦርነትና የእልቂት ዘመቻ ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ያው ጠላትና ወዳጅን መለየትና በተለይም ጠላት ማን እንደሆነ ማወቅና በዚህ ጠላት ላይ ማለምን ጠያቂ ይሆናል ማለት ነው:: ከነገረ ቀደም መወሰንና መደምደም ያለበት ይህ ነው:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ቅስም የሰበረውና በጎተ ሸንሽኖ ከፋፍሎ ሊያጫርሰው የሚሯሯጠው፤ መብት ያፈነው፤ ሀገሪቷን የዘረፈው፤ ሰላም ያሳጣው ወያኔ ነው:: ወያኔና ኢትዮጵያዊነት ከያኔውም እሳትና ጭድ የሆኑ በመሆናቸው በሞኝ ክንድ የዘ ዶ ጉድጓድ ይለካበታል በተባለው ዓይነት ልንሞኝ ካልሆነ በቀር ይህን ቡድን ኢትዮጵያዊ ወይም ለዚህ ሀገር

ጥቅም አደብ ገዝቶ ይቆማል ብለን ማሰቡም ጥፋት ይሆናል። በድንበር ጦርነቱ ጊዜ ይህን ዓይነት መሞኘት አንገቱን ቀና አድርጎ ቁጥሩ የማይናቅ ክፍል መለስ ዜናዊ ወደብ ሲያስመልስ እየታየው በከንቱም ሞቷል። በግንቦት 97ም ይህ አምባገነናዊ ቡድን በምርጫ ቢሸነፍ ሥልጣን ይለቃል ወይም የጡት አባቶቹ ልቀቅ ቢሉት ይቀበላል የሚል ብዥታ ሰፍኖ ለተከተለው ጉዳት የማይናቅ አስተዋፅኦን አድርጓል። ሀገርን ማዳን ስንል የሀገር ጠላት የወያኔ አገዛዝ ነውና ጠላትን ወዳጅ ብሎ መፈረጅ ሆነ ከእርሱም መተቃቀፉ የሚታሰብ መሆን የለበትም። በዚህ በኩል በንፁኃን ዜጎች ደም የተፃፈ ተመክሮ ተትረፍርፏልና ስህተትን መድገሙ ማጠየቂያ አይኖረውም።

ሀገራችንን ከወያኔ የጥፋት ተልዕኮ ለማዳን ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚሁ ግዳጅ መሰለፍ መቻል አለበት። ትንሽ ትልቁ ብሔረሰብ ሃይማኖትና ፆታ ሳይለይ ኢትዮጵያን ለማዳን በትግሉ መሳተፉ ወሳኝ ነው። መደረግ ያለበት ትግል ቀላል አይደለምና፥ መስዋዕትነትን ጠያቂም ነውና በሀገር አድን ትግሉ ዜጋዎች ይሳተፉ ዘንድ ማረጋገጥ ያሻል። ኢትዮጵያን እወድሻለሁ ያላት ሁሉ ሊሞትላት ዝግጁ በነበር የወያኔ መንጋ እንዲህ በሀገር ላይ ባልተጫወተ ነበር። ስለዚህም በተጨባጭ ማለትም በገቢር ለሀገር ዘብ ቋሚዎችን፥ ታጋዮችን ማፍራት ያስፈልጋል። በሕዝብ ላይ ባላቸው ንቀትና ወይም ከአስተሐቅሮ የሚመነጭ አመለከካት የተነሳ ሕዝብን እናውቅልሃለን ብለው ሊሰየሙበትና ሙትልንና እንግዛህ የሚሉት ጮሌዎችና የሥልጣን ባለቤቶች ነን ዘመናዊ ስዩመ አማሪካን ነን ባዮች አቀብቁበውና በዝተው ቢገኙም፤ ሀገር አድን ትግልን በአፍ ደረጃ ወይም በምላስ እያጀቡ፤ የሚሰብቁት ጦር ፈረንጅ የለገሳቸውን የምሁርነት ታርጋ ብቻ ይሆንና በተጨባጭ ትግሉ ላይ ተሰማርተው እያነሰ ወይም እየተደናገረ ትግሉ መጫጫቱ የታየና የሚታይም ነው። በበርቱልን ፈንታ በፀረ ወያኔ ትግል ያስመረረውን ማብጠልጠሉም ፈሊጥ ሆነና፤ በሰማዕታት ደም መቀለዱ የመሰልጠን መግለጫ ተባለና ስለ ትግል ወሬው ደርቶ ተጨባጩ ትግል ግን ደብዛው ተፋዘዘ ። ሕዝብ ለሀገሩ ሆ ብሎ ተነስቶ ሊታገል ዝግጁ ቢሆንም ሀገሪቷ የራሱ መመኪያና መከበሪያ መሆን መቻሏን ከወዲሁ ማመን መቻል አለበት። ማለትም ያለፉትን ሥርዓቶች ለመመለስ ወይም በናፍቆት አድሶ ለመትከል የሚደረጉ ጥረቶችን ሊያጅብ አይችልም፤ አይፈልግም። የዱሮውን ናፋቂና መላሾች ለሀገር አድን ትግሉ ባላንጣ ናቸው። ዜጎች በታሪካቸው ከሞላ ጎደል ሊኩሩ ቢችሉም--ቢገባም የቀድሞውን የጭቆና ዘመን ማስወገድ እንጂ መመለስ የነገይቷ ኢትዮጵያ ገፅታ ሊሆን አይችልም። አንዱን አምባገነን በሌላ የመተካቱ ቅዠት ሊደጋገም የሚፈለግ ካለመሆኑ ሌላ በሕዝብ ስም የሚሰየሙ ሞግዚቶችንም ማፈራረቁ ለውጥ ሊባል የሚችል አይደለም። ሕዝብም ባለሥልጣን የሚሆንባትን ኢትዮጵያ እንጂ የዛሬና የትላንቱን መንቲያ አገዛዝ የሚሻ አይደለም።

ስለዚህም የነገይቷ ኢትዮጵያ፤ የምናድናት ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መሆን አለባት። የሚያድኗትም ኃይሎች ዴሞክራሲያዊ መሆን አለባቸው እንጂ የሕዝብ ጠር የነበሩና የሆኑ አገዛዞች ቁንጮዎችና ቀንደኛ ወንጀለኞች ሊሆኑ አይጠበቅም። ሀገር አድን በሚል ሽፋን ትግሉ

*ከደፈረሰና ከቆሸሸ መጨረሻው አያምርም። ኢትዮጵያን እናድናለን ብለው ኢትዮጵያን እንደግል ንብረታቸው ሊይዟትና ሊፈነጩባት የሚከጅሉትን፥ የትላንቱን የጭቆና ሥርዓት በአዲስ መልክ ሊያሰፍኑ የሚመኙትን፥ በንፁሐን ደም የረጠበ እጃቸው ገና ያልደረቀንና ሕዝብን ይቅርታ ያልጠየቁትንና በተለይም ነገ ለህገሪቷ ዴሞክራሲን ሳይሆን ሲያስለቅሳት የባጀውን የገማ የገለማውን ሥርዓት የሚያመጡባትን በሀገር አድኑ ትግል ማቀፍ ትግሉን ከመጀመሪያው ማደናቀፍ መሆኑ መታወቅ አለበት። ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት እስከሆነ ድረስ የተጨቆነውም፥ ሆድ ብሶት የከረመውም፥ ሙሉ የዜግነት መብቴ አልተጠበቀም የሚለውም፥ ኢትዮጵያዊነቱን በቀና መንፈስ መጠራጠር የተያያዘውም፥ ጭቁኑና ድሃው በተለይ ገፈት ቀማሹ ብዙኃኑ ይታገልላታል፤ ይሞትላታል። የተጠላውን ለመመለስ ግን የሚታገል አይሆንም። ስለዚህም ኢትዮጵያን ለማዳን በዴሞክራሲያውያን በሚመራ ትግል ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚካሄድ ትግል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።*

*ግፍ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ እየፈሰሰባት ባለባት ሀገራችን፥ የወያኔ በደልና ጭቆና አስመርሮት ብዙኃኑ ተዋረድን፤ ተሰቃየን አያለ በሚጮህበት ሁኔታ ይህ አሸባሪ አገዛዝ 18ኛ ዓመቱን ሊያከብር ማቆብቆብ ባልቻለ ነበር። የኢትዮጵያ ብሥራትና ስርየት ጊዜ ባልፈጀ፤ የጠባቦች ዳንኪራ በአጭሩ በተቀጨና የጥፋት ዝናናባቸውም ወዲያውኑ ባቆመ ነበር። ይህ ግን አልሆነም። ለዚህም ምክንያቱ ምን መሆኑን በጥሞና መመርመር ያስፈልጋል። የተጓዝበት ጎዳና ወደ ፈለግነው ቦታና ዓላማ እያደረሰን አይደለምና ወይ በመንገዱ ወይ በመዳረሻው ላይ ያለውን ችግርና ጉድለት ማወቁ አስፈላጊ ይሆናል። ካለፉት የትግል ተመክሮዎች በትህትና መማር አማራጭ የለውም። አላወቅም አስገድሎ አያውቅም ነውና መማሩ ከመሰሪው ወያኔ ዋሻ የፖለቲካ ድንግል ሆኖ ገብቶ ከመጠቃቱ ያድናል። የወያኔን ጠላትነት አወቆ በፅናት መታገልን በምንም ምክንያት አለመተውንም ያስተምረናል። የታጋዩም ጎራ መፅዳት መጥራት እንዳለበት እንገነዘባለን። ዝንጀሮ በመጀመሪያ መቀመጫዬን አለች ቢባልም የዝ ጀሮ መቀመጫና ሀገር ከቶም ሊመሳሰሉና ሊነፃፀሩ አይችሉም። ሀገራችንን ማዳኑ መልሶ ሀገርን ለጥፋት መዳረግ እንዳይሆን ማዳን እንዴት፤ከማን ጋርና ለምን የሚለውን በሚገባ ማጤንና በትክክሉ መመለስ አለብን። ሀገር ማዳን ነውና ዋናው ሙቱና በኋላ እኛ ባፈተተን እንገዛችኋለን ለሚሉን ጭዳ መሆናችን ማብቃት አለበትም ማለት ነው። ኢትዮጵያ ትቅድም አለምንም ደም ኢትዮጵያን በደም ጎርፍ አቆርቁዟታል። የወያኔም ጦርነት ያብቃ፤ ሰላምና መረጋጋትም መጣ ልፈፋው መጨረሻው ለዘረኛው ቡድን ሕዝብን ሰለባ ማድርግ መሆኑ ያነው ነው። እንደገና ሊጭኑትና ሊጫወቱበት ያጩት ሕዝብ ከተገፋና ካመረረ የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊለማ ማለትን መገደዱ አይቀርም። ከዚህ የሚከተለውም ደግሞ ለዝንጀሮ መፈንጫም ጎጆ የማይተው ሊሆን ይችላልና ዘረኞቹም ዜጋም ሁሉ ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።*

*የወያኔ ጨለማ ጥቅጥቅ ያለ ቢሆንም ጭጋጉ እየገለጠ መምጣቱ አይቀሬ ነውና ነገ የሚፈነጥቀው ፀሐይ ለባሰ ድርቅ የሚዳርገን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለግን ኢትዮጵያን ማዳኑን ከዴሞክራሲ*

ጋር አጣምረን መያዝ ማካሄድ አለብን። ነጋ ጠባ አረመኔዎች እንዳይፈራረቁብን፤ ሐሳዊ መሲሁ ሁሉ ነቢይ መስሎ ገደል እንዳይከተን ቀንብር እንዳይጭንብን፤ እምቢኝ በቃ ብለን መነሳት መታገል አለብን ማለት ነው። በርዕዮት ልዩነትና ዝርዝር ሳንፈራቀቅ በመሠረታዊ ዴሞክራሲ ራዕይ ዙሪያ ና በኢትዮጵያዊነት በመያያዝ ፀረ ወያኔ ትግሉን ማፋፋምና ከግብ ማድረስ አሁንም ግዳጃችን ሆኖ ከፊታችን ተደቅኗል። ልዩ ልዩ የፖለቲካ ኃይሎች ስለ ዴሞክራሲ የሚደረድሩት ፍካሬም ምን ለመሆኑ ሕዝብ ነቅቶ ካለየ ካልመረመረ አፈ ጮሌዎች ትግሉን እያደናቀፉበት የሚፈልጋት ድል ቀን እየራቀችና ሀገር አዳኝ ነን ያሉት ሀገሩን የሚነጥቁት ሆነው ሳለ የሚጠቀሙበት ይሆናሉ። ሕዝብ ደሙን አፍሶ ነገም የደም ግብር የሚያስገብረው ሥርዓት እንዲመሠረትበት ተባባሪ መሆን የለበትም። ሀገርክን አድን የዴሞክራሲን ጉዳይ ግን አሁን አታንሳ የሚሉት ሆኑ፤ አልተማርክም አታውቅም እኛ እናውቅልኃለን፤ ልሂቆች የተማርንና ልንገዛህ የተመረጥን ነን የሚሉት ሆኑ፤ ያለፈውን መከራ የረሳ ይመስል የጥንቱን ያለፈውን ምድረ ገነት አስመስለው የሚያቀርቡት ሁሉ ለሕዝብ አይበጁም። ሀገርንም አያድኑም-- ለሀገር ጠንቅ ይሆናሉ እንጂ።

ኢሕአፓ ሀገርና ሕዝብን ነጥሎ ያያበት ቀን የለምና ዛሬም ሀገርን ማዳን ሲል ሀገርን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልሶ ማስረከብ በሚል ነው። እያዘመመ ያለው ወያኔ መንኮታኮቱ አይቀሬ ነውና ከዚያስ የሚለው ጥያቄ ለኢሕአፓ ወሳኝና ቀዳሚ ነው። ለሀገር ሲል ኢሕአፓ ደሙን ካፈሰሱትም ጋር ቢሆን አንጃ ግራንጃን ቂምን ትቶ አብሮ ሊሰራ ሊታገል የሞከረ ድርጅት ነውና በዚህ በኩል አጎደልክ ወቀሳን በዚህ ጉዳይ ላይ ማቅረቡ አግባብነት የለውም እንላለን። ድርጅቱ የቆመውና የሚታገልውም ለኢትዮጵያ ነውና፤ አለ ድርጅት ትግል ለድል አይበቃምና አባላቱና ደጋፊዎቹ ተንከባብክበው ይይዙታል። የትግል ተመክሮው የሚያስተምረው ሐቅ ግን ሀገርን ማዳን የሚቻለውና የሚገባው ከሐቀኛ ሀገር ወዳደች ጋር ፥ ከጭቁኑ ሕዝብ ጋር ሆኖ ብቻ ነው የሚል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ያደረገው ጉዞ ረጅም ነው። ዛሬ የአገዛዝ ለውጥና የሥርዓት ለውጥ ከሀገር ማዳን ጋር ተጣምሮ መጥቶበት ትግሉን ይበልጥ ከባድ አድርጎበታል። ላይችል አይሰጠውም ነውና ይህ ጀግና ሕዝብ ሀገሩንም ማዳን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንም እውን ማድረግ ይችላል ብሎ ኢሕአፓ በፅኑ ያምናል።

ኢትዮጵያ በጀግና ልጆቿ ትግል ትከበራለች!!